# ፕሮፌሰር ዶናልድ ሌቪንና ፖለቲከኞቻችን

**Wednesday, 10 March 2010**
በየማነ ናግሽ

ኢትዮጵያ አሁን ባለው የኢኮኖሚና የፖለቲካ ደረጃ ላይ እንድትገኝ ያደረጓት ሁኔታዎችን የሚተነትኑ ተመራማሪዎች፣ በርካታ መልካም የለውጥ ዕድሎች አምልጧታል ይላሉ፡፡

ይልቁንስ የተገኙትን እነዚህን አጋጣሚዎች ለአዎንታዊ ለውጦች አለመጠቀሚ ብቻ ሳይሆን፣ በተቃራኒው ወደ አሉታዊ ሁኔታዎች የሚመሩ ክንውኖች ተፈጽመውበትም ነበር ይላሉ፡፡ ምርጫ 2002 የአገሪቱንና የዜጎቿን የወደ ፊት የለውጥ ዕጣ ፈንታ ከሚወስኑ አጋጣሚዎች መካከል አንዱ እንደሆነ ስሙ እየተነሳ ነው፡፡

ባለፈው ሐሙስ ፕሮፌሰር ዶናልድ ሌቪን ከቺካጎ በቴሌ ኮንፈረንስ በቀጥታ ያደረጉት ንግግር የኢትዮጵያ ከፍተኛ ባለሥልጣናትና የኢትዮጵያ ተቃዋሚ ፓርቲዎች አመራሮችን አከራክሯል፡፡ ለኢትዮጵያ የፖለቲካ ቀውስ ብቸኛ መፍትሔው "መነጋገር" ብቻ ነው በሚለው የጸና አቋማቸው የሚታወቁት ሌቪን፣ ምርጫ 2002ም "የሚያመልጥ ዕድል" እንዳይሆን ስጋት አላቸው፡፡ ሌቪን ከዚህ በፊት አመለጡ የሚሉዋቸው የኢትዮጵያን ዕጣ ፈንታ በመወሰን ከፍተኛ ሥፍራ የሚሰጣቸው አምስት አጋጣሚዎች፣ በሁለቱ ወንድማማቾች መንግሥቱ ንዋይና ገርማሜ ንዋይ የተጠነሰሰው ያልተሳካ የመፈንቅለ መንግሥት ሙከራ፣ የ1966ቱ በደርግ የተቀለበሰው አብዮት፣ የ1983 ዓ.ም. የኢህአዴግ ድል፣ የ1990 ዓ.ም. የኤርትራ ወረራ እና የ1997ቱ ምርጫ ቀዳሚዎች ናቸው፡፡



የካህቁስሮ"ስቄ Ethiopia" እና የ "Wax and Gold" ደራሲ የሆኑት ሌቪን፣ የንግግራቸው አንኳር ጉዳይ፣ መጪው ምርጫ 2002ን የተመለከተ ነበር፡፡ ኢትዮጵያ በሚቀጥሉት 10 እና 20 ዓመታት ውስጥ ምን ትመስል ይሆን? ይህ ምርጫስ ኢትዮጵያን ወዴት ያመራታል? ያለፈው የአገሪቱ ታሪክ በቀጣዩ ምርጫ ላይስ ምን ዓይነት ተጽዕኖ ያሳድር ይሆን? የሚሉ ጥያቄዎችንም አንስተዋል፡፡

ሌቪን፣ የኢትዮጵያ ፖለቲካ በቂም በቀል የተሞላ ነው ከሚለው ይነሳሉ፡፡ እንደ እሳቸው እምነት፣ ይህንን ሁኔታ "የወጋ ቢረሳ የተወጋ አይረሳም" በሚለው የአማርኛ ተረት የገለጹት ሲሆን፣ "መላው የኢትዮጵያ ሕዝብ የተወጋ ነው" ብለዋል፡፡

ፕሮፌሰር ሌቪን፣ ባለፉት ዘመናት ኢትዮጵያ ውስጥ በፖለቲከኞች የተፈጸሙትን ስህተቶችና በአገሪቱ ታሪክ ላይ ያሳደሩትን ተጽዕኖ ይዘረዝራሉ፡፡ ኢትዮጵያውያን ከማንም በላይ ከራሳቸው ያለፈው ስህተት እንዲማሩም ይመክራሉ፡፡ "ምከረው፣ ምከረው እምቢ ካለ ግን መከራ ይምከረው" በማለት፡፡ "በአሁኑ ጊዜ መከራችሁ አልበዛም ወይ?" በማለት አገሬው ምን ያህል ካለፈው የኢትዮጵያ ታሪክ እየተማረ እንደሆነ በመጠየቅ፣ ወደ ዋናው ወቅታዊ ጉዳይ ይገባሉ፡፡

"አሁን ሥልጣን ላይ ያለው መንግሥት ብዙ ነገር አሳክቷል፡፡ ሆኖም፣ ውጭ ካለውና ውስጥ ካለው ሕዝብ ጋራ ሠርቶ ቢሆን ምን ያህል የበለጠ ነገር ማሳካት ይችል ነበር?" በማለት ከአንድ ኢትዮጵያዊ የተነገራቸውን አውርተውልናል፡፡

ኢትዮጵያውያን የሚለያዩባቸው በርካታ ጉዳዮች ያሉ ቢሆንም አንድ የሚያደርጓቸው መሠረታዊ ችግሮች አሉ ይላሉ ሌቪን፡፡ የምግብ እጥረት (ረሃብ"፣ የደን ጭፍጨፋ፣ በሽታዎች (ኤች አይቪ ኤድስ እና ወባ"፣ የኢነርጂ (ኃይል) እጥረት፣ የአዲሱ ትውልድ ቀቢጸ ተስፋነት፣ ወዘተ ይጠቃቅሳሉ፡፡

የምርጫ 2002 ተስፋ? ጠ/ሚ መለስን ጨምሮ የመንግሥት ከፍተኛ ባለሥልጣናት ምርጫውን ሰላማዊ፣ ነጻና ዴሞክራሲያዊ ለማድረግ ቃል እየገቡ ነው፡፡ በአሁኑ ወቅት ተፈጻሚነቱ ጥያቄ ውስጥ እየገባ ቢሆንም፣ ተቃዋሚዎችና ገዢው ፓርቲ የተፈራረሙትና አዋጅ ሆኖ የጸደቀው የምርጫ ሥነ ምግባር ተስፋ የሚጣልበት ነው፡፡ ምርጫ ቦርድ አቅሙን ለማሳደግና "ገለልኝነቱን ለመጠበቅ" የሚያደርገው ጥረት የሚበረታታ ነው፡፡ እነዚህ ሒደቶች ለሌቪን ግምገማ አዎንታዊ ግብአቶች ናቸው፡፡

በአንጻሩ ግን እነዚህን ተስፋ የሚጣልባቸው ክንውኖች የሚያጨልሙ ምልክቶች እየታዩ ነው፡፡ ከተለያዩ ወገኖች የሚነሱ ግጭትን የሚቀሰቅሱ ንግግሮች (Inflamatory መ"ሮ"ስቂስታ"ቋ"፣ "በእያንዳንዱ ሰው አእምሮ ውስጥ ያለው ከምርጫው ምንም አዎንታዊ ነገር ያለመጠበቅ አመለካከት" እና የመሳሰሉ በጎ ያልሆኑ የቅድመ ምርጫ ምልክቶችን በማጣቀስ፣ ምርጫው ነጻና ፍትሐዊ ይሆን? የሚለውን ተስፋ እንዳያጨልመው እሰጋለሁ ብለዋል፡፡ በመሆኑም ይሄንንም ዕድል እንደ 97ቱ የሚያበላሹ ባሕርያት እየታዩ ነው የሚለው ንግግራቸውን ሌቪንያጠናክራሉ፡፡

በተለይ በቅርቡ በትግራይ ክልል አድዋ (እምባሰነይቲ ወረዳ) የተፈጸመው የአቶ አረጋዊ ገ/ዮሐንስ ግድያ ምርጫ ምን ሊመስል እንደሚችል የሚያሳይ መጥፎ ድባብ የሚያላብስ ነው ይላሉ፡፡ ሌቪን ቀጣዩን ምርጫ በማስመልከት፣ ይሄ ዓመት 2010 ነው ወይስ 1960 (እ.ኤ.አ". በማለት ያነጻጽሯቸዋል፡፡ ማንኛውም ስህተት ሥልጣን ላይ ወዳለው መላከክ [Blaming the negus፣ አሉባልታ ላይ መመስረትና በእሱ ተመስርቶ የተዛባ አመለካከት (Distorted Perception) መያዝ፣ ቀጥተኛና ግልጽ ንግግር አለማድረግ፣ [Wax and gold ፣ ማሰር፣ መገዳደልና መፎካከር ረማን ከማን ያንሳልሪ ወዘተ. በሁለቱም ዘመናት ያሉት ባሕርያት ይሉዋቸዋል፡፡ ጠ/ሚኒስትሩ በፖሊሲያቸው ላይ ጥያቄ የሚያነሱ ማናቸውም ሰዎች "ፀረ ዴሞክራሲ"፣ "ፀረ ሕዝብ"፣ ካርካሽካ - - - "ራስ ወዳዶች" ማለታቸው፣ በአንጻሩ ደግሞ፣ አንድ የተቃዋሚ ፓርቲ ቃል አቀባይ ኢህአዴግን እንደ ሰይጣን ማጥላላት (Demonization) ወዘተ. የቆዩ ባህሎች አሁንም ቀጥለዋል ይላሉ፡፡

ሌቪን እንደሚሉት፣ በተለያዩ ወገኖች የተለያዩ ጥፋቶች እየተፈጸሙ ቢሆንም፣ መንግሥት "የአንበሳውን ድርሻ" ይወስዳል፡፡ በተለይ የተቃዋሚ ታርቲዎች አባላትና ደጋፊዎችን ማዋከብና ማንገላታት፣ የምርጫው ሒደት ላይ የሚፈጸሙ ስህተቶችና ክፍተቶችን በመሙላት ፕሬስ ከፍተኛ ሚና እንደሚጫወት፣ ነገር ግን በጠላትነት እየተፈረጀ ስለመሆኑ፣ ግልጽነትና ተቀራርቦ አለመነጋገር፣ የመሰብሰብና የመደራጀት መብቶች አለመከባበር፣ ወዘተ ይዘረዝራሉ፡፡ ገዢው ፓርቲ ኅብረተሰቡን በሴቶች፣ በወጣቶች ፎረሞችና ሌሎች ሊጎች እያጨናነቀ ስለመሆኑ፣ ሁሉን ሰው አባል ለማድረግ የሚያደርው ሩጫ በዘላቂነት ዴሞክራሲ ለመገንባት ያለውን ቁርጠኝነት አጠያያቂ ያደርገዋል ይላሉ፡፡ ሌቪን፣ ኢህአዴግን ብቻ አልወቀሱም፤ ተቃዋሚዎችም የአካሄድ ለውጥ ያስፈልጋቸዋል ይላሉ፡፡ መግሥትንና ተቋማቱን ዕውቅና መስጠት፣ ቅሬታቸውን ለዓለም አቀፉ ኅብረተሰብ ከመናገር ይልቅ አገር ውስጥ ላሉ ሕጋዊ አካሎች ማቅረብ፣ መንግሥትን ከማጥላላትና ለማሸነፍ ብቻ ከመሮጥ ለመተጋገዝና ለመነጋገር መሞከር እንዳለባቸው ይመክራሉ፡፡

ተቃዋሚዎች ኢህአዴግን ከማጥላላትና ከመውቀስ ውጪ ለአገሪቱ ምን ሊያደርጉ እንዳሰቡና ምን ፕሮግራም እንደያዙ "አዎንታዊ" መልዕክታቸውን ቢያስተዋውቁ የሕዝብ ተአማኒነትን ያገኛሉ ይላሉ፡፡ ሁሉንም ፖለቲከኞች ኃይልን ከመጠቀም፣ ከመሰዳደብ፣ ከመጠቋቆር፣ ከመኮራረፍ ፖለቲካ ወጥተው የመነጋገርና የመወያየት ባህል እንዲያዳብሩም ይመክራሉ፡፡

"የመጠፋፋትና የጥላቻ  ተቃውሞ በሃሳብና በአመክንዮ ፉክክር ቢተካ ሁሉም ተጠቃሚ ይሆናል፡፡ የምርጫው ሒደት ጥሩ ከሆነ ሁሉም አሸናፊዎች ይሆናሉ፤ መጥፎ ከሆነ ግን ማንም አሸናፊ አይሆንም፡፡"

ሌቪን ሃሳባቸውን የሚያጠናቅቁት፣ ኢትዮጵያ ለአፍሪካ አርአያ እንድትሆን፣ በውጭ የሚኖሩ ዜጎቿን እንድትጠራና፣ የመነጋገርና የመወያየት ባህል እንድታዳብር ሃሳብ በመስጠት ነው፡፡

ዶ/ር ነጋሶ ጊዳዳ የኢትዮጵያ የፖለቲካ ባህልን አስመልክተው በሰጡት አስተያየት፣ የአክሱም ሥልጣኔን አድንቀው የሃበሻ የቆየ የመገዳደልና የወንድ የበላይነት ባህል ከፍተኛ ተፅዕኖ እያሳደረ መሆኑን ተናግረዋል፡፡ የኦሮሞ ዴሞክራሲን ረየገዳ ሥርዓትሪ እንዲሁ አድንቀዋል፡፡

ዶ/ር ነጋሶ፣ ሥልጣንና ሃብት "በአንድ ቡድን ቁጥጥር ሥር በወደቀበት ሁኔታ እንዴት ተቻቻሉ ይሉናል?" በሚል ላቀረቡት ጥያቄ፣ ሌቪን አደገኛ የተዛባ አመለካከት ብለውታል፡፡ ኦሮሞዎች በአቢሲኒያ ወይም በኢትዮጵያ ቅኝ ግዛት ተገዝተናል የሚሉት እንዴት ብለው ይገልጹታል? በማለት፣ በተለይ ሦስቱም ትግራይ፣ አማራና ኦሮሞ ለአሁኗ ኢትዮጵያ መገንባት የየበኩላቸውን አስተዋጽኦ ማበርከታቸውን ግን በአጽንኦት አስረድተዋል፡፡

የኢትዮጵያ መንግሥት የኮምዩኒኬሽን ጉዳይ ጽ/ቤት ሚኒስትር አቶ በረከት ስምኦን በበኩላቸው፣ የኢህአዴግ መንግሥት ይሄ ነው የሚባል የሚያስወቅስ ነገር እንዳልሰራ፣ ይልቁንም የኢትዮጵያ ሕዝብን "ዘር እያጠፋ" ከነበረው ደርግ መንጋጋ አላቆ በዴሞክራሲና በልማት ጎዳና ላይ የመራ ነው የሚል አስተያየት ሰጥተዋል፡፡ ተቃዋሚዎችን ማዋከቡን በተመለከተም ተቃዋሚዎች ያሉትን ሁሉ እንደ እውነት የመውሰድ አባዜ እንዳለ ተናግረዋል፡፡ "ከ97 ምርጫ በኋላ የተደረጉ ለውጦችን በውል የተገነዘቡ አይመስልም" በማለትም የሌቪንን ንግግር ተችተዋል፡፡ "በተለይ ይሄንን መንግሥት የአናሳ ብሔር (Minority) አስመስሎ ማቅረብን እንደ ማንቋሸሽ አድርገን እንገነዘባለን" ብለዋል፡፡ "አሁንም ይህ አመለካከት የትም የሚያደርስ አይደለም፡፡ ካለፈው የእርስ በርስ መወቃቀስ መውጣት ያለብን ይመስለኛል፡፡"

ቀጣዩን ምርጫ በተመለከተም፣ የ97 ቀውስ የተፈጠረው በውጭ ጣልቃ ገብነት መነሻ መሆኑን በመጥቀስ፣ "በውጭ ኃይሎች ላይ ከመንጠልጠል የምንወጣበትን ለእኛ ኢትዮጵያውያን ምን ይመክሩናል?" በሚል ጥያቄ ሃሳባቸው አጠናቀዋል፡፡

የወቅቱ የመድረክ ሊቀመንበር ፕሮፌሰር በየነ፣ "በፕሮፌሰር ሌቪን ሃሳብ አልስማማም" በማለት ነበር አስተያየታቸውን የጀመሩት፡፡ በተለይ የኢትዮጵያ ዕጣ ፈንታን መተንተን ያለበት "መልካም ዕድሎች አምልጧታል" በሚል ሳይሆን፣ "ፈተናዎችን በመቋቋም ኖራለች" የሚለውን የአማራጭ ሃሳብ አቅርበዋል፡፡ "አመለጡ የተባሉ መልካም ዕድሎች ፈተናዎች ነበሩ፡፡ አሁንም ቢሆን ምርጫው መልካም ዕድል ሳይሆን ማለፍ ያለብን ከባድ ፈተና ብለን ነው የምንገነዘበው" ብለዋል፡፡ መድረክከድርድር ረግጦ ወጣ በሚል ለተነሳውም "የምርጫ ሕጉ በመጽደቁ ምንም ተቃውሞ የለንም፣ እኛ ግን በዋና ጉዳዮች ላይ እንነጋገር ብለን ነበር፣ ኢህአዴግ አፈነገጠ እንጂ" የሚል ምላሽ ሰጥተዋል፡፡ "እንነጋገርባቸው ያልንባቸው መሠረታዊ ችግሮች አሁንም አደገኛ ሆነው ቀጥለዋል፡፡ የሕግ የበላይነት እየተጣሰ ነው፣ ስለ ምርጫ ጨዋታ የጋራ ስምምነት ላይ መድረስ አልተቻለም፣ አባሎቻችን እየታሰሩ፣ እየተገደሉ፣ ከስራ ገበታቸው እየተባረሩ ነው፡፡ የእኔ ጥያቄ መጪው ምርጫ ዕድል ነው ወይስ ፈተና ይዞ የሚጠብቀን?" ብለዋል፡፡

ፕሮፌሰር ዶናልድ ሌቪን በፕሮፌሰር  የምርጫ ትንታኔ እስማማለሁ ብለዋል፡፡
የመኢአድ የውጭ ግንኙነት ኃላፊ አቶ ያዕቆብ ልኬ፣ በፕሮፌሰሩ ንግግር ላይ ምንም ተቃውሞ እንደሌላቸው፣ መጪው ምርጫም በኢትዮጵያ ሰላማዊ የሥልጣን ሽግግር ለማድረግ የመጨረሻ ዕድል ሆኖ መተንተን እንዳለበት ተናግረዋል፡፡

"ምርጫ 2002 ለኢትዮጵያ ሕዝብም፣ ለኢህአዴግም፣ ለተቃዋሚዎችም የመጨረሻ ዕድል ነው፡፡ የምርጫ ሥነ ምግባር ሕጉንም ተፈጻሚነት እንጠብቃለን አቶ ያዕቆብ አስረድተዋል፡፡

ዶክተር መረራ በበኩላቸው፣ በሌቪን ንግግር የማይስማሙባቸው ጉዳዮች ያሉ መሆቸውን በመግለጽ፣ የገዢውን ፓርቲ ብቸኛ የበላይነት የሚያረጋግጥ "ዜሮ ድምር ፖለቲካ" እየተከተለ ነው ብለዋል፡፡ "ከዚህ የብቻ የበላይነት ፍላጎት የምንወጣበት ፣ማጂክ ፎርሙላ፣ (አስማታዊ ቀመር) ሊሰጡን ይችላሉ ወይ?" የሚል ጥያቄ መሰል አስተያየት ሰጥተዋል፡፡

የኢህአዴግ ሥራ አስፈጻሚ አባልና የመንግሥት ተጠሪ አቶ ኃ/ማርያም ደሳለኝ በበኩላቸው፣ ውንጀላዎችን እንደ እውነት መውሰድ ተገቢ አይደለም" በሚል አስተያየታቸውን ሰጥተዋል፡፡ ስለ አቶ አረጋዊ ገ/ዮሐንስ ግድያ በተመለከተ ከፕሮፌሰር ሌቪን የተሰነዘረው ሃሳብ አልጣማቸውም፡፡ "እኛ በቂ መረጃ አለን፡፡ ግድያው ከፖለቲካ ጋር ምንም ግንኙነት የለውም፡፡ የበለጠ አጣርተው እንዲናገሩ እጠይቅዎታለሁ፡፡"

አቶ ኃ/ማርያም፣ መንግሥታቸው የመነጋገርና የመወያየት ባህል እያዳበረ መሆኑን፣ የመቻቻል ባህል ግን እንደሚወራው መተግበሩ ቀላል እንዳልሆነ፣ ይሄም ከውጭ ተነግሯቸው ሳይሆን ከራሳቸው ከውስጥ አምነውበት እየሰሩ እንደሆነ ሃሳባቸውን ገልጸዋል፡፡ "ይሄ ከውጭ ያስገባነው ሳይሆን ከራሳችን ጥረት የሚመነጭ ነው፡፡ ይሄንን ሰው ሁሉ ሊገነዘበው ይገባል፡፡"

አቶ ኃ/ማርያም፣ በማከልም ከዶክተር መረራ የቀረበው "ማጂክ ፎርሙላ" ንገሩን የሚለውን ሃሳብ ተችተዋል፡፡ "ማጂክ ፎርሙላ ውይይትን ረግጦ አለመውጣትና ከውስጥ የሚመነጭ እንጂ ከውጭ የሚበረከት አይደለም" በማለት፡፡

አቶ በረከት ስምኦን፣ በፕሮፌሰር ዶናልድ ሌቪን አዲስ ነገር ጋዜጣን አስመልክቶ የተሰጠው አስተያየት ስህተት መሆኑን ተናግረዋል፡፡ መንግሥታቸው ከጋዜጠኞች ጋር አዲስ ግንኙነት መጀመሩንና ራሱን ተደራሽ ማድረጉን በመግለጽ፣ መንግሥት በአዲስ ነገር ላይ የወሰደው ምንም ዓይነት እርምጃ ወይም ያደረገው ተጽዕኖ የለም ብለዋል፡፡ "አዲስ ነገር የተዘጋበትን ምክንያት እኛ እናውቃለን፡፡ በአዲስ ዘመን መተቸቱ ግን ምንም ወንጀል አይደለም፡፡ መንግሥትን ሲተች የሚውል ጋዜጣ፣ በጋዜጣ ተተቸሁ ብሎ የሚያኮርፍ ከሆነ ምን ማለት ይቻላል?" ብለዋል፡፡

የመኢአድ ፕሬዚዳንት ኢንጂነር ኃይሉ ሻውል በበኩላቸው፣ ሕገ መንግሥቱንም ሆነ የምርጫ ሥነ ምግባር ደንቡ መሠረታዊ ችግር እንደሌለባቸው ገልጸው፣ "ችግሩ መጻፉ ላይ አይደለም፣ መተግበሩ ላይ ነው" ብለዋል፡፡

"ወረቀት ላይ ማስፈር ከባድ አይደለም፣ የተጻፈውን መፈጸም ግን አልተቻለም" በማለት ኢህአዴግን ወቅሰዋል፡፡

Source: Reporter – Amharic Version